# ከትምህርት ቤቱ ነርስ ቢሮ

*Kristin Shiraishi RN, BSN, PHN*
*Samuel Tucker Elementary School*
*Email: kristin.shiraishi@acps.k12.va.us Phone: 703-933-6307*

## ጥቂት ማሳሰቢያዎች እና ጤናማ ጥቆማዎች ከትምህርት ቤቱ ነርስ!

**ሕክምና ፤** በተቻለ መጠን የመድሀኒት አሰጣጥ ከትምህርት ሰዓት ውጭ መሆን አለበት። ነገር ግን ልጅዎ በትምህርት ሰዓት መድሐኒት መውሰድ ካለበት እባክዎን “**መድሀኒት ለመስጠት ፍቃድ መስጫ**” ቅፅ በልጅዎ ሃኪም ተሞልቶ ለትምህርት ቤቱ ነርስ መሰጠት ያለበት መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ። ሁሉም መድሐኒቶች ( በሃኪም ትእዛዝ ወይም ያለትእዛዝ) በዋናው በመጀመሪያው የመድሀኒት መያዣ ውስጥ፣ ታሽገው እና የልጁ ስም ከላይ ተፅፎበት መላክ አለባቸው። ያለ ሀኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ መድሐኒቶች (ታይላኖል፣ ኢቦሮፊን ወዘተ..) ያለሀኪም ትእዛዝ ሊሰጡ አይችሉም። **Epi-Pens፣ የመተንፈሻ (Inhalers) እና በመርፌ የሚሰጡ መድሐኒቶች ለየብቻቸው ፍቃድ ፎርም ያስፈልጋል።** ሁሉም መድሐኒቶች በወላጅ/አሳዳጊ በእጅ ለነርስ ቢሮ መሰጠት ይኖርበታል። ልጆች በቦርሳቸው መድሐኒት ወደ ትምህርት ቤት እንዲያመጡ መደረግ አይኖርበትም።

**ህመም/አደጋ፤** በትምህርት ሰዓት ልጅዎ ከታመመ ወይም አደጋ ካጋጠመው እርሱ/ሷ በትምህርት ቤቱ ነርስ ይታያሉ። ትንሽ የተጋጠ ካለ ለማፅዳት ሳሙና እና ውሃ መጠቀም ይቻላል። ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ነርስ በሄደ ቁጥር ለእርስዎ በየቀኑ እንዲያውቁት አይደረግም። ነገር ግን ልጅዎ የከፋ ህመም/አደጋ ካጋጠመው ለእርስዎ ለማሳወቅ የሚቻለውን ሁሉ ይደረጋል። እባክዎን ሁሉም የስልክ ቁጥር እና የጤና መረጃ ዓመቱን በሙሉ ወቅታዊ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ።

የሰውነት ሙቀት 100 ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሰውነት ሙቀት ያላቸው ልጆች ወደቤት ይላካሉ። እባክዎን ልጅዎ ከትኩሳት(ከ100 ዲግሪ በታች) ለ24 ሰዓታት ትኩሳት የሚያበርድ <u>መድሐኒት ሳይጠቀሙ</u> ነፃ እስከሚሆኑ ድረስ በቤት እንዲቆዮ ያድርጉ። ሌላ የሚጠረጠር ተላላፊ በሽታዋች ምልክት ያላቸው ልጆች በትምህርት ቤት ነርስ ውሳኔ ወደቤት እንዲሄዱ ይደረጋል። ልጅዎ በተላላፊ በሽታ የተያዘ መሆኑ ከታወቀ ለምሳሌ፤ ፍሉ ፣ ቺክን ፖክስ(ፈንጣጣ) ወይም ስትቲፕ ስሮት እባክዎን ለትምህርት ቤቱ ያሳውቁ። ልጅዎ በሀኪም ከታየ በኋላ ከሐኪም የሚሰጡ ትእዛዞችን ኮፒ ለትምህርት ቤቱ ነርስ መስጠት እንዲያውቅ ማድረግ ጠቃሚ ነው። **የሆስፒታል ቆይታ፣ ብዙ ቀናት መቅረት እና የከፋ ህመም እና/ወይም አደጋዎች የሀኪም ወረቀት ማቅረብ ያስፈልጋል።** እንዲሁም መደረግ ስለሚኖርባቸው ወይም ሌላ ገደቦችን (የሚኖር ከሆነ ) እና ገደቡ የሚቆይበት ጊዜ የጊዜው መጠን ዝርዝር ትእዛዞችን መቅረብ ይኖርበታል። እባክዎን ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ **በፊት** ይህን መረጃ ለትምህርት ቤቱ ነርስ ይስጡ።

**ከትምህርት ቤት ቀሪ መሆን፤** አባክዎን ልጅዎን ትኩሳት፣ ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ ያልታወቀ የቆዳ ሽፍታ፣ የአይን ኢንፌክሽን፣ ከባድ ሳል ወይም መተንፈስ ችግር፣ የመራመድ ችግር፣ አቅማ ማጣት ካለው በቤት ውስጥ እንዲቆይ ያድርጉ። ወደ ዋናው ጽህፈት ቤት ይደውሉ ልጅዎ ቀሪ ከሆነ እና ልጅዎ በጤና ባለሞያ የታየ ከሆነ ይንኑ ያሳውቁ።

**የምግብ አለርጂ/የውጭ ምግብ፤** ወላጆች የልጅዎን የምግብ አለርጂ ለትምህርት ቤት ነርስ እና ለአስተማሪ ማሳወቅ <u>**እጅግ በጣም አስፈላጊ**</u> ነው ። ሁሉም ተማሪዋች ደህንነት ለማስጠበቅ ለልጅዎ ምግብ ከሚሆነው ከምሳ እና ጤናማ ስናክ ውጭ የውጭ ምግብ ወደ ትምህርት ቤት **እንዳይመጣ** ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ይጠይቃል ። ***የምግብ አለርጂ ህይወትን አደጋ ወደሚጥል ሁኔታ የመቀየር አቅም አለው።*** ወላጆች መፅሀፍት፣አርሳስ ወይም ሌላ ከምግብ ውጭ የሆኑ እቃዋችን ለልደት ቀን ፣ ፓርቲዋችና የዓመቱ መጨረሻ ዝግጅት ላይ ለማምጣት ቢያስቡ ይመረጣል። * እባክዎን ያስታውሱ፤ ምግብ መምረጥ እንደ አለርጂ አይቆጠርም።

**ከባድ የጤንነት ሁኔታዎች፤** የትምህርት ቤቱ ነርስ አስፈላጊ የተለየ ከባድ የጤና ሁኔታዎች በተመለከተ እንደ አስም፣ የስኮር በሽታ፣አለርጂ እና የሚጥል በሽታ ፣ ሲክል ሴል በሽታ፣ ካንሰር፣ እና ሌሎች የጤና ሁኔታዋች ከተማሪዋችና ከቤተሰቦች ጋር በመተባበር ይሰራሉ። ወላጆች ስለተማሪያቸው የተለየ ጤና ሁኔታ እና ልጃቸው በትምህርት ቤት በሚቆይበት ወቅት ስለሚያስፈልገው የጤና አጋዥ መሳሪያ (ማለትም፣ ድጋፍ መርኩዝ፣ ስፕሊንትስ፣ ለእግር መሄጃ መደገፊያ ወዘተ...) ለትምህርት ቤቱ ነርስ እንዲያሳውቁ ይጠየቃሉ ። እባክዎን ስለልጅዎ የተለየ ጤና ሁኔታ፣ የእንቅስቃሴ ገደብ፣ ስለምግብ አሰጣጥ፣ ሌላ በትምህርት ቤት ሰዓት የሚያስፈልግ ሁኔታ ወይም አሰራር አስፈላጊ ከሆነ ከልጅዎ ሀኪም ማስታወሻ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።

**ተባይ፤** የፀጉር ተባይ በየአካባቢው የሚኖር የማህበረሰብ ችግር ነው። አደገኛ አይደሉም እና በሽታም አያስተላልፉም። የተባይ ችግር ያላባቸው ተማሪዋች ተማሪዋቹ በእለቱ ህክምና እንዲያገኙ የትምህርት ቤቱ ነርስ ለወላጅ ማሳሰቢያ ይልካል። በቤት ውስጥ ከታከሙ **<u>በኋላ</u>** በቀጣዮ ቀን ልጆች ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላሉ።

**ልብስ፤** አልፎ አልፎ ልጆች በልብሳቸው ላይ ሊሸኑ ወይም ልብሳቸውን ሊቀዱ ይችላሉ። ልጆች የጠበባቸውን ልብሶች በስጦታ መልክ ለሰጡ ወላጆች ምስጋና ይግባቸውና እኛ <u>አንዳንድ</u> ጊዜ ተማሪዋች ወደቤት ለብሰው እንዲሄዱ እናደርጋለን። እባክዎን እኒዚህን ልብሶች በተቻለ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ ያድርጉ ለሌሎች ተማሪዋች አገልግሎት እንዲወሉ። ፒ.ቲ.ኤ. ጥቂት አዳዲስ የውስጥ ቡታንታ በስጦታ አምጥተዋል እነሱ መመለስ አይኖርባቸውም። የእርስዎ በተከታታይ የሽንት ችግር ካለበት እባክዎን ለግሉ እንዲያገለግል ተጨማሪ ልብስ በቦርሳው ያድርጉ።

**ማጠሪያ ምርመራ ፤** በመዋእለ ህጻናት ያሉ ሁሉም ተማሪዋች፣ የ3ኛ ክፍል ፣ 7ኛ ክፍል እና 10ኛ ክፍል ተማሪዋች እንዲሁም በትምህርት ቤት ክልሉ አዲስ የሆኑ ተማሪዋች የአይን እና የጆሮ ምርመራ በትምህርት ቤት ያደርጋሉ። የተለየ ሁኔታ በምርመራው ከተገኘ ወላጆች በደብዳቤ/በኢሜል እንዲያውቁት ይደረጋል። እባክዎን ስለልጅዎ ጉዳይ እና በምርመራ ሂደት የሚያሳስብዎ ነገር ካለ የትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ይገናኙ። በምርመራ ቀን በበጎ ፈቃደኝነት ለመስራት ፈቃደኛ ከሆኑ እባክዎን ከትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ይገናኙ።

**ማንኛውም ጥያቄዋች ወይም የሚያሳስብዎ ጉዳይ ካለዎት ከእኔ ጋር ይገናኙ፤**

**ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሆነ የትምህርት ዓመት እንዲኖርዎ እንመኛለን!**